ያ ነፍሴ በእጁ በሆነችው ጌታዬ እምላለሁ! ከናንተ በፊት የነበሩትን ህዝቦች መንገድ ትከተላላችሁ።'

ከአቡ ዋቂድ አል-ለይሢይ (ረዲየሏሁ ዐንሁ) - አላህ መልካም ሥራቸውን ይውደድላቸውና - እንደተላለፉት: "የአላህ መልክተኛ (የአላህ ሶላትና ሰላም በእርሳቸው ላይ ይስፈንና) ወደ ሑነይን የወጡ ጊዜ 'ዛቱ አንዋጥ' በምትባል የአጋርያን ዛፍ በኩል አለፉ። በርሷ ላይ (በረከትን በመፈለግ) መሳሪያዎቻቸውን ያንጠለጥሉባት ነበር። ሶሐቦችም 'የአላህ መልክተኛ ሆይ! ለነርሱ ‹ዛቱ አንዋጥ› እንዳላቸው
ለኛም (የምናንጠለጥልበት) ‹ዛቱ አንዋጥ› አድርግልን።' አሉ። ነቢዩም (የአላህ ሶላትና ሰላም በእርሳቸው ላይ ይስፈንና) እንዲህ
አሉ 'ለአላህ ጥራት ተገባው! ይህ (የተናገራቹት) የሙሳ ህዝቦች {ለእነርሱ አማልክት እንዳላቸው ለእኛም አምላክን አድርግልን።}
[አል አዕራፍ: 138] ብለው እንደተናገሩት ነው። ያ ነፍሴ በእጁ በሆነችው ጌታዬ እምላለሁ! ከናንተ በፊት የነበሩትን ህዝቦች
መንገድ ትከተላላችሁ።'"
[ሶሒሕ ነው።] [ቲርሚዚና አሕመድ ዘግበውታል።]

የአላህ መልክተኛ (የአላህ ሶላትና ሰላም በእርሳቸው ላይ ይስፈንና) ወደ ሑነይን ወጡ። ሑነይን: በጧኢፍና መካ መካከል የሚገኝ ሸለቆ ነው። ከርሳቸውም ጋር የሚጓዙ በቅርብ ወደ ኢስላም የገቡ የተወሰኑ ሶሐቦች ነበሩ። "ዛቱ አንዋጥ" ማለትም የመንጠልጠያ ባለቤት በምትባል ዛፍ በኩል አለፉ። ዛፊቱ አጋርያን ያልቋትና መሳሪያዎቻቸውንና ሌሎች ነገሮችንም በረከትን በመፈለግ የሚያንጠለጥሉባት ዛፍ ነበረች። ከመልክተኛው (የአላህ ሶላትና ሰላም በእርሳቸው ላይ ይስፈንና) ለነርሱ በረከትን ለመፈለግ መሳሪያዎቻቸውን የሚያንጠለጥሉበት የርሷ አምሳያ ዛፍ እንዲያደርጉላቸው ፈለጉ። ይህም የሚፈቀድ ነገር ስለመሰላቸው ነው። ነቢዩም (የአላህ ሶላትና ሰላም በእርሳቸው ላይ ይስፈንና) ይህንን ንግግራቸው እያወገዙ አላህን በማላቅ ተስቢሕ አደረጉ። ይህ ንግግር የሙሳ ህዝቦች {ለእነርሱ አማልክት እንዳላቸው ለእኛም አምላክን አድርግልን።} በማለት ለሙሳ የተናገሩትን ንግግር እንደሚመስልም ተናገሩ። የሙሳ ህዝቦች ጣኦት የሚያመልክን በተመለከቱ ጊዜ አጋርያን ጣኦት እንዳላቸው ለነርሱም ጣኦት እንዲኖራቸው ፈለጉ። ይህ ግን የነርሱን መንገድ መከተል ነው። ቀጥለውም ነቢዩ (የአላህ ሶላትና ሰላም በእርሳቸው ላይ ይስፈንና) ይህ ህዝብ የየሁዶችንና የክርስቲያኖችን መንገድ እንደሚከተልና የነርሱን ድርጊት እንደሚፈፅም በማስጠንቀቅ መልኩ ተናገሩ።

http://sunnah.global/hadeeth/am/show/5927